የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፺
አዲስ አበባ–ጳጉሜ ፬ ቀን ፲፱፻፺፭

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

9th Year No. 90
ADDIS ABABA-9th September, 2003

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፭/፲፱፻፺፭ ዓ·ም·
የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ገጽ ፪ሺ፫፻፸

CONTENTS

Proclamation No. 365/2003
Federal Prisons Commission Establishment Proclamation ........................................ Page 2370

### አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፭/፲፱፻፺፭
### የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን
### ማቋቋሚያ አዋጅ

ለኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ–መንግሥት ታማኝና በሕገ መንግሥቱ መሠረት ለሚወጡ ሕጎች ተገዥ የሆነ የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ተቋም ማቋቋም በማስፈለጉ፣

ማረሚያ ቤቶች የፍርድ ቤት ውሳኔዎችን በመፈጸም ሂደት ታራሚዎችን የመጠበቅ እና የማረም ተግባራትን በማከናወን ወንጀልን በመከላከል ረገድ የበኩላቸውን ተገቢ አስተዋጽኦ ማድረግ የሚጠበቅባቸው በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ–መንግሥት አንቀጽ ፶፭/፩/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፭/፲፱፻፺፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

### *ROCLAMATION NO. 365/ 2003*
### *A PROCLAMAION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF FEDERAL PRISONS COMMISSION*

*WHEREAS,* it is necessary to set up an organ of Federal Prisons that adheres to the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and that is committed to the laws enacted on the basis of the Constitution;

WHEREAS, in due course of implementing judical decisions, need to undertake the functions of the custody, reformation and rehabilitation of prisoners in order to duly contribute their part in crime prevention;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

### PART ONE
### GENERAL

1) Short Title

This proclamation may be cited as the ''Federal Prisons Commission Establishment Proclamation No. 365/ 2003.''

2. *Definition*

In this Proclamation, unless the context requires otherwise:

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 4.40

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፩· "ኮሚሽን" ማለት በዚህ አዋጅ የተቋቋመ የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን ነው፤

፪· "የጋራ ጉባኤ" ማለት የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን እና የክልል ማረሚያ ቤቶች ኃላፊዎች የጋራ ጉባኤ ማለት ነው፤

፫· "ሚኒስቴር" እና "ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተላቸው የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር እና የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስትር ነው፤

፬· "ማረሚያ ቤት" ማለት በፍርድ ቤት ውሳኔ መሠረት የሚላኩ ታራሚዎች የተወሰነባቸውን የእሥራት ቅጣት የሚፈጽሙበት፣ የሚታረሙበት ፣ እንዲሁም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የሚላኩ ውሳኔ እስከሚያገኙ እንዲቆዩ የሚደረግበት የፌዴራል ማረሚያ ተቋም ነው፤

፭· "ታራሚ" ማለት በሕግ ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት የተወሰነበትን የፍርድ ውሳኔ በማረሚያ ቤቶች ውስጥ በመፈጸም ላይ የሚገኝ የሕግ ታራሚ ሲሆን በማረሚያ ቤት በቀጠሮ እንዲቆይ የተወሰነበትንም ይጨምራል፤

፮· "የማረሚያ ጠባቂ" ማለት መሠረታዊ የሆነ የማረሚያ የጥበቃ ሙያ ሥልጠና ተሰጥቶት በኮሚሽኑ ተቀጥሮ የሚሠራ የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን አባል ነው።

## ክፍል ሁለት
## ስለፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን መቋቋም

፫· መቋቋም

፩· የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን ከዚህ በኋላ "ኮሚሽን" እየተባለ የሚጠራ ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌዴራል መንግሥት አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

፪· ኮሚሽኑ በሕግና በሙያው የሚኖረው ነፃነት እንደተጠበቀ ሆኖ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል

፬· የኮሚሽኑ ዋና መሥሪያ ቤት

፩· የኮሚሽኑ ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ይሆናል፤

፪· ከዚህ በፊት በፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ስር ሲተዳደሩ የነበሩት ማረሚያ ቤቶች በኮሚሽኑ ስር ሆነው ይዋቀራሉ።

፫· ኮሚሽኑ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት የሚያከናውኑ አካላትን በማናቸውም ቦታ ማቋቋም ይችላል።

፭· ዓላማ

የኮሚሽኑ ዓላማ ታራሚዎችን ተቀብሎ መጠበቅ ፣ ለታራሚዎች የተሐድሶ አገልግሎት በመስጠት የአስተሳሰብና የስነ ምግባር ለውጥ እንዲያመጡ እንዲሁም ሕግ አክባሪ ፣ ሰላማዊና አምራች ዜጎች እንዲሆኑ ማድረግ ነው።

፮· የኮሚሽኑ ሥልጣንና ተግባር

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩· በፍርድ ቤቶች ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ መሠረት የሚላኩለትን ታራሚዎች በመቀበል ይጠብቃል፣ ያርማል ፣ እንዲሁም ከፍርድ ቤት የሚሰጡ ሌሎች ትእዛዞች ይፈጽማል፤

፪· ታራሚዎችን ፍርድ ቤት ያቀርባል፤

፫· የታራሚዎችን ጤንነት ይጠብቃል፣ በዚህ አዋጅ በሚወጣው ደንብ መሠረት ታራሚዎች ነፃ ሕክምና ፣ ምግብና መጠለያ እንዲያገኙ ያደርጋል። ለታራሚዎች አካላዊና አዕምሮአዊ እንክብካቤ አስፈላጊ የሆኑ ተግባሮችን ያከናውናል፣ አገልግሎቶችን ይሰጣል፣ ዝርዝሩ ኮሚሽኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፤

፬· ታራሚዎች ከተለቀቁ በኋላ ራሳቸውን ለማስተዳደር የሚችሉና ለሕግ ተገዢ እንዲሆኑ ለማድረግ የሚያስችል የቀለም ትምህርት ፣ የሙያ ሥልጠና ፣ ማኅበራዊ አገልግሎትና የምክር አገልግሎት ይሰጣል። ዝርዝሩ በደንብና በመመሪያ ይወሰናል፤

1) "Commission" means the Federal Prisons Commission established under this Proclamation.
2) "Joint Council" means Joint Council of the Commission of Federal Prisons and Regional Prison heads.
3) "Ministry" and "Minister" means, respectively, Ministry of Federal Affairs and Minister of Federal Affairs.
4) "Prison" means a federal correctional institution where prisoners sentenced by court serve their sentences, are reformed and rehabilitated; and where remand prisoners are held in custody until verdict.
5) "Prisoner" means a convicted prisoner serving a sentence passed by a court authorized by law; and shall also refer to a person detai· ed upon judicial remand.
6) "Prison Warden" shall mean members of the Federal Prisons Commission employed after having obtained basic prison warden-ship training.

## PART TWO
## *ESTABILISHMENT OF FEDERAL PRISONS COMMISSION*

3. *Establishment*
   1) The Federal Prisons Commission, hereinafter referred to as "Commission," is hereby established and granted its own juridical personality as an organ of the Federal Government.
   2) Without prejudice to its legal and professional independence, the Commission shall be accountable to the Ministry.

4. *Head Office*
   1) The Head Office of the Commission shall be in Addis Ababa;
   2) Prisons that were administered under Federal Prison Administration shall be incorporated into the Commission.
   3) The Commission may establish, in any place, organs that undertake the powers and duties entrusted to the Commission.

5. *Objectives*

   The objectives of the Commission shall be to admit and ward prisoners, and provide them with reformative and rehabilitative service in order to enable them make attitudinal and behavioral changes, and become law-abiding, peaceful and productive citizens.

6. *Powers and Duties of the Commission*

   The Commission shall have the following powers and duties.
   1) ward and reform the prisoners it admits upon judical sentences or warrants; and shall also enforce other judical decisions;
   2) take prisoners to court;
   3) maintain prisoners' health care; and provide prisoners with free medical treatment, food and shelter in accordance with the Regulations to be issued on the basis of this Proclamation; undertake and encourage tasks, services and activities necessary for the physical and mental well-being of prisoners; particulars shall be determined by the Directives to be issued by the commission;
   4) provide prisoners with academic education, vocational training, and social work services and counseling services to facilitate their post-release rehabilitation and respect for the law; particulars shall be determined by regulations and directives;

፭· በፍርድ ቤት ሲታዘዝ ታራሚዎችን ከፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ወደ ክልል ማረሚያ ቤቶች ወይም ከአንድ ማረሚያ ቤት ወደሌላ ማረሚያ ቤት አጅቦ ያደርሳል፤

፮· ታራሚዎች በማረሚያ ቤት ቆይታቸው የማረሚያ ቤቱን የሥነ ሥርዓት መመሪያ በመጣስ ለሚፈጽሙት ጥፋት በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው ደንብ ወይም መመሪያ መሠረት የሥነ ሥርዓት ቅጣቶችን ይወስናል፤ ይፈጽማል፤

፯· በሀገር አቀፍ ደረጃ ታራሚዎችን በሚመለከት መረጃዎችን እና ስታስቲኮችን ያሰባስባል ፤ ያጠናቅራል፤

፰· ታራሚዎች በሚያሳዩት የባህሪይ ለውጥ በሕግ መሠረት፤
ሀ) በአመክሮ ወይም
ለ) በይቅርታ፤
እንዲፈቱ ሥልጣን ለተሰጠው አካል ሀሳብ ያቀርባል።

፱· ኮሚሽኑ ለሥራ አስፈላጊ የሆነ የማረሚያ ጥበቃ አባላት ይመለምላል፤ ይቀጥራል፤ ያሰለጥናል፤ እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ የሆኑት ሠራተኞች ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፤

፲· የኮሚሽኑን ሠራተኞች የሙያ ብቃት ለማሳደግ በሀገር ውስጥ እና በውጭ ሀገር የሥልጠና ዕድሎችን ያመቻቻል፤

፲፩· የታራሚዎችን አጠባበቅና አያያዝ ለማሻሻል ፤ የማረሚያ ጥበቃ አባላትና ሠራተኞችን ሙያ ብቃትና አገልግሎት በሀገር አቀፍ ደረጃ ተመሳሳይነት ያለውና ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን ለማድረግ የሚረዱ ጥናቶችን ያከናውናል፤

፲፪· ለክልል ማረሚያ ቤቶች የሙያና የቴክኒክ እንዲሁም የምክር ድጋፍ ይሰጣል፤

፲፫· ውል ይዋዋላል፤ በራሱ ስም ይከሳል፤ ይከሰሳል።

፯· የኮሚሽኑ አቋም

፩· ኮሚሽኑ፦
ሀ) በፌዴራል መንግሥት የሚሾሙ አንድ ኮሚሽነር እና አንድ ምክትል ኮሚሽነር፤
ለ) ኮሚሽነሩን ፤ ምክትል ኮሚሽነሩንና የዋና መምሪያ ኃላፊዎችን ያቀፈ የሥራ አመራር ጉባኤ ፤ እና
ሐ) ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ የማረሚያ ጥበቃ አባላትና የመንግሥት ሠራተኞች ይኖሩታል።

፪· የኮሚሽኑ አደረጃጀት ዝርዝር በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፱ ንዑስ አንቀጽ /፮/ መሠረት ይወሰናል።

፰· የኮሚሽኑ የሥራ አመራር ጉባዔ ሥልጣንና ተግባር

የሥራ አመራር ጉባዔው፦

፩· የታራሚዎችን አጠባበቅ፤ አያያዝ እና የማረሚያ ቤቶችን አስተዳደር ለማሻሻል የሚረዱ ሀገር አቀፍ የፖሊሲ፤ የስትራቴጂና የስታንዳርዳይዜሽን ጥናቶችን በመመርመር ከአስተያየት ጋር ለፌዴራል ማረሚያ ኮሚሽንና ለክልል ማረሚያ ቤቶች ኃላፊዎች የጋራ ጉባዔ እንዲቀርቡ ያደርጋል፤

፪· የኮሚሽኑን አደረጃጀት፤ አወቃቀርና አሠራር የሚመለከቱ ጥናቶችን ይመረምራል፤ ሊወሰዱ የሚገባቸውን እርምጃዎች ከአስተያየት ጋር ለሚኒስትሩ ያቀርባል፤

፫· የኮሚሽኑን የሥልጠና ዕቅድ ያዘጋጃል፤

፬· የኮሚሽኑን ረቂቅ በጀት ያዘጋጃል፤ በፌዴራል መንግሥት እንዲፀድቅለትም በኮሚሽነሩ በኩል ለሚኒስትሩ ያቀርባል፤

፭· የኮሚሽኑን ዓመታዊ ዕቅድ፤ ኦዲትና ሥራ አፈፃፀም ይገመግማል፤ ከአስተያየት ጋር ለሚኒስትሩ ያቀርባል፤

፮· በኮሚሽኑ እና በክልል ማረሚያ ቤቶች መካከል መልካም የሥራ ግንኙነት እንዲኖር ጥረት ያደርጋል።

5) up on court order, transfer prisoners with warden escort from a Federal Prison to a Regional Prison, or from any prison to another.
6) determine and implement disciplinary measures, in accordance with the Regulations or Directives to be issued under this Proclamation, against prisoners who infringe prison rules while in custody;
7) gather and organize country-wide data and statistics about prisoners;
8) submit to the competent organ recommendations of:
   (a) parole, or
   (b) pardon,
   so that prisoners be released in accordance with the law, on the basis of their behavioral reform;
9) recruit, employ, train and administer the necessary prison wardens and other necessary staff;
10) facilitate opportunities for training in Ethiopia or abroad in order to upgrade the professional competence of the Commission's employees;
11) undertake studies that can help improve the custody and treatment of prisoners, and that facilitate country-wide similarity and standardization in the professional competence and service of prison wardens;
12) provide professional, technical and advisory assistance to Regional Prisons;
13) enter into contracts; sue in its own name; or, be sued.

7. *Structure of the Commission*

1) The Commission shall have:
   (a) a commissioner and a deputy commissioner appointed by the Federal Government;
   (b) management council of the commission is composed of commissioner, deputy commissioner and the head of departments: and
   (c) prison warden and civil service staff necessary for its functions.
2) The particulars of organizational set-up of the Commission shall be determined pursuant to Article 9 (6) of this Proclamation.

8. *Powers and Duties of the Management Council of the Commission*

The Management Council Shall:
1) examine studies on countrywide policy, strategy, and standardization towards the improvement of the custody and treatment of prisoners, and towards improving prison administration; and thereupon submit the studies with recommendations, to the Joint Council of Federal Prison Commissioners and Regional Prison heads;
2) examine studies on the organization, structure and operation of the Commission and submit recommendations of necessary measures to the Minister;
3) prepare training plans of the Commission,
4) prepare the draft budget of the Commission; and submit same to the Minister through the commissioner, for approval by the Federal Government
5) evaluate the Commission's annual plan, audit report and performance; and submit same; with proposals, to the Minister;
6) make efforts towards good relations between the Commission and Regional Prison Commissions.

፱· <u>የሚኒስትሩ ሥልጣንና ተግባር</u>

ሚኒስትሩ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡

፩· የኮሚሽኑን አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴዎች ይከታተላል፡

፪· የኮሚሽኑ ኮሚሽነር እና ምክትል ኮሚሽነር ሹመት እንዲጸድቅለት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ያቀርባል፡

፫· የኮሚሽኑን ዋና መምሪያ ኃላፊዎች ምደባ ያፀድቃል፡

፬· የኮሚሽኑን ዓመታዊ ዕቅድ፡ ረቂቅ በጀት፡ ሪፖርትና የሥራ አፈፃፀም ከአስተያየት ጋር ለፌዴራል መንግሥት ያቀርባል፡

፭· የታራሚዎች መብት መከበሩንና በአግባቡ ጥበቃ መደረጉን እንዲሁም ታርመውና አምራች ዜጋ ሆነው መውጣታቸውን ይከታተላል፡

፮· በኮሚሽኑ የሚቀርቡትን የአደረጃጀት፡ እና የአቅም ግንባታ መርሐ ግብር ጥናቶች ይመረምራል፡ ያፀድቃል፡

፯· የኮሚሽኑን የሥራ ብቃትና ውጤታማነት ለማሳደግ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፡ የቁጥጥር ሥራ ያከናውናል፡

፰· ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚረዱ አስፈላጊ እርምጃዎች ይወስዳል።

፲· <u>የኮሚሽነሩ ሥልጣንና ተግባር</u>

፩· ኮሚሽነሩ ተጠሪነቱ ለሚኒስትሩ ሆኖ የኮሚሽኑን ሥራ በበላይነት ይመራል፡ ያስተባብራል፡

፪· የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚሽነሩ፡—

ሀ) የዋና መምሪያ ኃላፊዎች ምደባ እንዲፀድቅለት ለሚኒስትሩ ያቀርባል፡

ለ) የኮሚሽኑን መተዳደሪያ ደንቦች ያስፈጽማል፡

ሐ) ለሥራ አስፈላጊ የሆነ የማረሚያ ጥበቃ አባላት ይመለምላል፡ ይቀጥራል፡ ያሰለጥናል፡ እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞችን ይቀጥራል፡ ያስተዳድራል፡

መ) በፌዴራል ማረሚያ አቤቱታ ሰሚ አካል እና በዲሲፕሊን ኮሚቴ የሚሰጡ ውሳኔዎች በይግባኝ ሲቀርቡለት ይወስናል

ሠ) የኮሚሽኑን ዓመታዊ የሥራ እቅድና ረቂቅ በጀት አዘጋጅቶ ለሚኒስትሩ ያቀርባል፡ በፌዴራል መንግሥት ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፡

ረ) ለኮሚሽኑ በተፈቀደለት በጀት መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፡ የኦዲትና የኢንስፔክሽን ሥራዎች እንዲሠሩ ያደርጋል፡

ሰ) የኮሚሽኑን አደረጃጀት፡ አሠራርና አቅም ግንባታ የሚመለከቱ ጥናቶች፡ የታራሚዎችን አጠባበቅና አያያዝ ለማሻሻል የሚረዱ ጥናቶች፡ እንዲሁም የማረሚያ ጥበቃ ሙያና አገልግሎት ተመሳሳይነት ያለውና ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችሉ ጥናቶች እንዲከናወኑ ያደርጋል፡

ሸ) በኮሚሽኑ እና በክልል ማረሚያ ቤቶች መካከል መልካም ግንኙነት እንዲኖር ጥረት ያደርጋል፡

ቀ) የኮሚሽኑን የአመራር ጉባዔ በሰብሳቢነት ይመራል፡

በ) ኮሚሽኑን አስመልክቶ የውጭ ግንኙነት ያደርጋል።

፲፩· <u>የምክትል ኮሚሽነሩ ሥልጣንና ተግባር</u>

፩· ምክትል ኮሚሽነሩ፡—

ሀ) የኮሚሽኑን ተግባራት በማቀድ፡ በማደራጀት፡ በመምራትና በማስተባበር ኮሚሽነሩን ይረዳል፡

ለ) በኮሚሽኑ መዋቅር መሠረት የሥራ ክፍፍሎች በማድረግ ከኮሚሽኑ ዘርፎች ከፊሉን ይከታተላል፡

9. *Powers and Duties of the Minister*

The Minister shall have the following powers and duties,

1) follow-up the overall activities of the Commission;
2) submit to the Prime Minister the nomination of the Commissioner and Deputy Commissioner of the Commission for appointment;
3) approve the appointment of head department of the Commission;
4) submit the annual work plan, draft budget, report and performance of the Commission to the Federal Government with recommendations;
5) follow up that the rights of prisoners are respected and their custody secured, and that prisoners are enable to be reformed and productive citizens upon their release;
6) examine and approve studies submitted by the Commission on organizational and capacity building programs;
7) take appropriate steps to enhance the competence and effectiveness of the Commission; and undertake tasks of supervision;
8) take the steps necessary for the implementation of this Proclamation.

10. *Powers and Duties of the Commissioner*

1) The Commissioner shall be accountable to the Minister, and shall direct and coordinate the tasks of the Commission.
2) Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article the Commissioner shall:
   (a) submit the nomination of department head to the Minister for approval;
   (b) direct the implementation of the Administrative Regulations of the Commission;
   (c) recruit, employ and train the necessary prison warden, employ and administer other necessary staff;
   (d) render decisions on appeals lodged against decisions made by the Federal Prisons Complaints Hearing Organ and Discipline Committee;
   (e) prepare and submit the work plan and the draft budget of the Commission, submit same to the Minister, and implement them upon approval by the Federal Government;
   (f) effect expenditures on the basis of the budget allocated to the Commission, and cause audit and inspection to be conducted;
   (g) cause studies to be conducted with regard to the Commission's organization, and capacity building; as regards improvement of the custody and treatment of prisoners; and towards facilitating the operational similarity and standardization of prison warden service;
   (h) make efforts towards good relations between the Commission and Regional Prison
   (i) preside over the meetings of the Management Council of the Commission;
   (j) undertake external relation in matters pertinent to the Commission,

11. *Powers and Duties of the Deputy Commissioner*

1) The Deputy Commissioner shall:
   (a) assist the Commissioner in planning, organizing, directing and coordinating the functions of the Commission;
   (b) follow up the performance of a part of Commission's departments pursuant to the division of labour made as per the structure of the Commission;

ሐ) ኮሚሽነሩ በማይኖርበት ጊዜ ተክቶት ይሠራል፣
መ) በኮሚሽነሩ ተለይተው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል።

፪· ምክትል ኮሚሽነሩ ተጠሪነቱ ለኮሚሽነሩ ይሆናል።

፲፪· <u>በጀት</u>

የኮሚሽኑ በጀት በፌዴራል መንግሥት ይመደባል።

፲፫· <u>የሂሣብ መዛግብትን የሂሳብ ምርመራ</u>

፩· ኮሚሽኑ የተሟላና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል፣

፪· የኮሚሽኑ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ።

## <u>ክፍል ሦስት</u>
## <u>ስለ ፌዴራል ማረሚያ ጥበቃ አስተዳደር</u>

፲፬· <u>ለማረሚያ ጥበቃ አባልነት የሚያበቁ መመዘኛዎች</u>

፩· በፌዴራል ማረሚያ ጥበቃ አባልነት ለመመልመል ፈቃደኛ የሆነ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የሚከተሉትን መመዘኛዎች በሙሉ ማሟላት ይኖርበታል፦

ሀ) ለኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ–መንግሥት ተገዥ የሆነ፣
ለ) ለማረሚያ ጥበቃ አባልነት ለመመልመል የሚያበቃ የትምህርት ደረጃ፣ አካላዊ ብቃት እና የተሟላ ጤንነት ያለው፣
ሐ) መልካም ሥነ ምግባር ያለው፣
መ) በፍርድ ቤት የተወሰነ የወንጀል ጥፋተኛነት የፍርድ ሪኮርድ የሌለው፣
ሠ) ዕድሜው 18 ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆነ፣
ረ) የማረሚያ የጥበቃ ሙያ ሥልጠናን ያጠናቀቀ።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚደረገው ምልመላ የፆታ ፣ እንዲሁም የብሔሮች ፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ሚዛናዊ ተወጽኦ ያካተተ ይሆናል።

፫· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት የተመለመለ ማንኛውም ዜጋ የፖለቲካ ድርጅት አባል የሆነ እንደሆነ በማረሚያ ጥበቃ ሲቀጠር የፖለቲካ ድርጅት አባልነቱን መተው ይኖርበታል።

፲፭· <u>ቃለ መሐላ ስለመፈፀም</u>

ለማረሚያ ጥበቃ ሥራ የተቀጠረ ማንኛውም ምልምል ለፌዴራሉ ሕገ መንግሥት ታማኝ በመሆን የተጣለበትን ሕዝባዊ አደራና ሙያዊ ኃላፊነት ለመወጣት ቃለ መሐላ ይፈጽማል። የቃለ መሐላው ይዘት በደንብ ይወሰናል።

፲፮· <u>የአገልግሎት ዘመን</u>

፩· የማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል የግዴታ አገልግሎት ዘመን ሰባት ዓመት ይሆናል። ዝርዝር አፈጻጸሙ በደንብ ይወሰናል፣

፪· የማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል ቅጥር ከሚከተሉት መካከል በማናቸውም ምክንያት ይቋረጣል፦

ሀ) በሞት፣
ለ) በደንቡ መሠረት የስንብት ጥያቄ ቀርቦ ተቀባይነት ሲያገኝ፣
ሐ) በሐኪሞች ቦርድ በተረጋገጠ ሕመም ወይም የአካል ጉዳት ለሥራው ብቁ ሳይሆን ሲቀር፣
መ) በፍርድ ቤት በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘና በደንቡ መሠረት ወንጀሉ ለሥራው ብቁ አያደርገውም ተብሎ ሲወሰን፣ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፣
ሠ) በሥራ አፈጻጸም ወይም ዲሲፕሊን ጥፋት፣

(c) act in place of the Commissioner in the absence of the latter;
(d) perform other duties that may be expressly assigned to him by the Commissioner.

2) The Deputy Commissioner shall be accountable to the Commissioner.

12. *Budget*

The budget of the Commission shall be allocated by the Federal Government.

13. *Books of Accounts and Audit*

1) The Commissioner shall keep complete and accurate books of accounts.
2) Books of Accounts and financial documents of the Commission shall be audited annually by the Auditor General, or by an auditor designated by the Auditor General.

## PART THREE
## *ADMINISTRATION OF THE FEDERAL PRISONS WARDEN*

14. *Requirements for prison warden recruitment*

1) Any Ethiopian who volunteers to be recruited as a member of the Federal Prisons Commission shall cumulatively fulfill the following:
   (a) Adherence to the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;
   (b) The educational standard, physical fitness and good health required upon recruitment for prison warden;
   (c) Good conduct;
   (d) No record of criminal conviction by a court of law;
   (e) Attainment of eighteen years of age or above;
   (f) Completion of prison wardens' training.
2) The recruitment to be made under Sub-Article (1) of this Article shall also consider the equitable representation of gender, nations nationalites and peoples.
3) Any citizen recruited in accordance with Sub-Article 1 of this Article shall, if he is a member of a political party, withdraw from his political party membership upon his employment as a prison warden member.

15. *Oath*

Every recruit employed as a prison warden shall take oath of loyalty to the Constitution in carrying out the public confidence and the professional responsibility entrusted to him. The content of the oath shall be determined by regualtions.

16. *Term of service*

1) The term of obligatory service of every prison warden shall be seven years. The particulars of implementation shall be determined by regulations.
2) The employment of any prison warden shall terminate on any one of the following grounds:
   (a) Upon death;
   (b) When a request for release, submitted in accordance with the Regulations is accepted;
   (c) Due to unfitness for his job on account of illness or physical injury verified by a medical board;
   (d) Due to judical conviction in a criminal offence, which, in accordance with the Regulations, renders him ineligible for his job; particulars shall be determined by regulations;
   (e) Owing either to inefficiency reports or discriplinary fault;

ረ) በጡረታ ሲገለል።

፲፯· መብት

፩· ማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል፦

ሀ) በፌዴራል መንግሥት በሚፀድቅ የደመወዝ ስኬል መሠረት ደመወዝ ያገኛል፤

ለ) በኮሚሽኑ የመተዳደሪያ ደንብ መሠረት ቀለብ፣ ልዩ ልዩ አበሎች፣ የደንብ ልብስና የሕክምና አገልግሎት ያገኛል፤

ሐ) በጡረታ ሕግ መሠረት የጡረታ መብት ይኖረዋል፤

መ) ሥራውን በተገቢው መንገድ በመወጣት ላይ እያለ ለሚደርስበት ተጠያቂነት በመሥሪያ ቤቱ ወጪ የጥብቅና አገልግሎት ያገኛል፤ ዝርዝር አፈጻጸሙ በደንብ ይወሰናል፤

ሠ) ከሥራው ጋር በተያያዘ ሁኔታ በደረሰበት ጉዳት ምክንያት ሙሉ ወይም ከፊል የመሥራት ችሎታውን በዘላቂነት ያጣ የማረሚያ ጥበቃ አግባብ ባለው የጡረታ ሕግ የተሰጠው መብት ይከበርለታል።

፪· ማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል፦

ሀ) የበላይ ኃላፊዎችን በአግባቡ የመጠየቅ ፣ ስህተት ሲያይ የመጠቆም እና ችግሮችን በውይይት የመፍታት መብት አለው፤

ለ) የሥልጣን ተዋረድን ጠብቆ አቤቱታ ማቅረብ ይችላል።

፲፰· ግዴታ

ማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል፦

፩· በሕገ መንግሥቱና ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ ድንጋጌዎች መሠረት የተረጋገጡትን ሰብዓዊ መብቶችና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ሙሉ በሙሉ በማክበር እንዲሁም በሌሎች አግባብ ባላቸው ሕጎች መሠረት ሥራውን የማከናወን፤

፪· የማረሚያ ጥበቃ ሥራውን ሲያከናውን ማንነቱን የሚገልጽ መታወቂያ የማሳየት ፣ ግዴታ አለበት።

፲፱· የጡረታ መውጫ ዕድሜ

ማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል በጡረታ የሚገለልበት ዕድሜ ጣሪያ አግባብ ባለው የጡረታ ሕግ መሠረት ለመንግሥት ሠራተኞች የተወሰነው የጡረታ መውጫ ዕድሜ ይሆናል።

፳· ስለ ፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አቤቱታ ሰሚ

በኮሚሽኑ ውስጥ አቤቱታ የሚሰማ የፌዴራል ማረሚያ ኮሚሽን አቤቱታ ሰሚ አካል ይቋቋማል ፣ ዝርዝሩ ኮሚሽኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

፳፩· ስለ መተዳደሪያ ደንብ

የማረሚያ ጥበቃ አባሎች መተዳደሪያ ደንብ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ይወጣል።

## ክፍል አራት
## ስለታራሚዎች አያያዝ

፳፪· መርህ

፩· ታራሚዎች ሰብዓዊ ክብራቸውን በሚጠብቁ ሁኔታዎች የመያዝ መብት አላቸው፤

፪· የታራሚዎች አያያዝ፣ ታራሚዎቹ የተወሰነባቸውን ቅጣት ጨርሰው ሲወጡ ሕግ አክባሪ ሆነው ራሳቸውን በራሳቸው ለማስተዳደር የሚያስችላቸው መሆን ይኖርበታል፤

፫· በፍርድ ቤት ቀጠሮ ላይ ያሉ እንዲሁም የፍትሐብሔር ታራሚዎች ከወንጀል ድርጊት ነፃ እንደሆኑ ተቆጥረው በወንጀል ቅጣት ከተወሰነባቸው ታራሚዎች ተለይተው መያዝ ይኖርባቸዋል።

፳፫· ታራሚን ስለመቀበል

በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ካልሆነ በስተቀር ኮሚሽኑ ማንኛውንም ሰው በማረሚያ ቤት እንዲቆይ መቀበል የለበትም።

(f) Upon retirement.

17. *Rights*

1) Every prison warden shall be entitled to:

(a) Salary according to the scale approved by the Federal Government;

(b) rations, various allowances, uniforms, and medical service in accordance with the Administrative Regulations of the Commission;

(c) retirement pension rights in accordance with pension laws;

(d) the services of an attorney at law, at the Commission's expense, for liabilities incurred while carrying out his task within the scope of his duties; particulars of implementation shall be determined by regulations;

(e) the benefits stipulated under the relevant pension laws, where he, in relation to his duties, sustains injuries that permanently cause his total or partial disability to work.

2) Every prison warden

(a) shall, upon incidence, have the right to forward appropriate questions to his superiors, indicate wrongs and, resolve problems through discussion;

(b) may lodge complaints through the appropriate hierarchy.

18. *Duties*

Every prison warden shall:

1) perform his duties by fully respecting the human rights and democratic rights enshrined in the Constitution and the international instruments adopted by Ethiopia, and in accordance with other relevant laws;

2) show an identity card that verifies his identity while carrying out his duties.

19. *Age of Retirement*

The age of pension retirement for any prison warden shall be same as that of civil servants as determined by the relevant pension lwas.

20. *Copmplaints Hearing Organ of Federal Prisons*

Complaints Hea.ing Organ of Federal Prisons Commission shall be established; the particulars shall be determined by the Directives to be issued by the Commission.

21. *Administrative Regulations*

Federal Prisons 'Wardens' regulations shall be issued by the Council of Ministers.

## PART FOUR
## *TREATMENT OF PRISONERS*

22. *Principle*

1) Prisoners shall have the right to be treated conditions of respect for human dignity.

2) The treatment of sentenced prisoners shall facilitate their post-release respect for law and their rehabilitation towards self-supporting reintegration into society.

3) Remand and civil prisoners shall not be persumed as offenders, and shall be entitled to treatment different from convicted prisoners.

23. *Admission of Prisoners*

No person shall be admitted into custody by the Commission without court warrant.

፳፬· ልዩነት ማድረግ የተከለከለ ስለመሆኑ

በታራሚዎች መካከል በፆታ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ አመለካከት፣ በብሔር ብሔረሰብ አባልነት ወይም በማኅበራዊ ምንጭ ልዩነት ማድረግ የተከለከለ ነው።

፳፭· ታራሚዎችን በፈርጅ ለይቶ ስለመያዝ

፩· ሴት ታራሚዎች ከወንድ ታራሚዎች ሙሉ በሙሉ የተለዩ ክፍሎች ይኖራቸዋል፣

፪· ሁኔታው በፈቀደ መጠን ታራሚዎች፣ በዕድሜያቸው፣ በፈጸሙት ወንጀልና በሌሎች ተመሳሳይ ምክንያቶች ተለይተው መያዝ ይኖርባቸዋል።

፳፮· የታራሚዎች ክፍሎች ሁኔታ

፩· ታራሚዎች የሚኖሩባቸው ክፍሎች እና ግቢያቸው በጤና ላይ ጉዳት የማያስከትሉ፣ ንፁህ አየርና በቂ ብርሃን የሚያገኙ መሆን ይኖርባቸዋል።

፪· የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የታራሚዎች መኖሪያ ክፍሎች ሲዘጋጁ ታራሚው በሚያሳየው የባህርይ ለውጥና በወንጀል ድርጊት የመፀፀት ሁኔታ አኳያ ለይቶ ለመጠቀም የሚያስችሉና ታራሚዎችን በቀና ተወዳዳሪነት መንፈስ ወደመታረምና ተሃድሶ የሚያተጉ ሊሆኑ ይገባል።

፳፯· ስለምግብና የጤንነት እንክብካቤ

ታራሚዎች በተቻለ መጠን ጤናቸውን ለመጠበቅ የሚያበቃቸውን በቂ ምግብና አስፈላጊውን የሕክምና አገልግሎት በነፃ ማግኘት ይኖርባቸዋል።

፳፰· ሕፃን ልጅ ስላላት ሴት ታራሚ

፩· ለልጁ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ፣ ዕድሜው ከአሥራ ስምንት ወራት ያልበለጠና የእናቲቱ የቅርብ ክትትል የሚያስፈልገው ሕፃን ከሴት ታራሚ እናቱ ጋር አብሮ ማረሚያ ቤት ውስጥ ሊቆይ ይችላል፣

፪· ኮሚሽኑ ለልጁ ጤንነትና እንክብካቤ አስፈላጊውን የማድረግ ኃላፊነት አለበት፣

፫· የእናቲቱ የእሥር ቆይታ በልጁ አካላዊ ወይም ሥነ ልቦናዊ አቋም ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድር ሆኖ ሲገኝ ሕፃኑ አሳዳጊ ወይም ሞግዚት እንዲያገኝ ኮሚሽኑ ሁኔታዎችን ያመቻቻል።

፳፱· ከጎብኚዎች ጋር ስለመገናኘት

ታራሚዎች ከትዳር ጓደኞቻቸው፣ ከቅርብ ዘመዶቻቸው፣ ከጓደኞቻቸው፣ ከሐኪሞቻቸው፣ ከሕግ አማካሪዎችና ከሃይማኖት አባቶች ጋር የመገናኘት መብት አላቸው፣ ዝርዝሩ ኮሚሽኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

፴· ስለመታሠርና ዝውውር መረጃ የማስተላለፍ መብት

ማንኛውም ታራሚ መታሠሩን ወይም በማናቸውም ምክንያት ከታሠረበት ተቋም ወደ ሌላ ተቋም መዛወሩን ወዲያውኑ ለቤተሰቦቹ ወይም ለሚፈልገው ሰው የመናገር መብት አለው።

፴፩· በሥራ ስለማሠማራትና ስለ ፈቃድ

፩· በፍርድ ቤት የተወሰነበትን ቅጣት በማረሚያ ቤት በመፈፀም ላይ ያለ ማንኛውም ታራሚ ከችሎታውና ከሙያው ጋር የሚስማማና ጤንነቱን የማይጎዳ ተመጣጣኝ ሥራ እንዲሠራ ይደረጋል፣ በኮሚሽኑ በሚወጣ መመሪያ መሠረት እንደሁኔታው ለሥራው ክፍያ ያገኛል፣

፪· ታራሚዎች በማረሚያ ጥበቃ አባል አጃቢነት ለልዩ ልዩ ማኅበራዊ ችግሮቻቸው ማቃለያ ፍቃድ የሚያገኙበት ሁኔታ በመመሪያ ይወሰናል።

24. *Prohibition of Discrimination*

No adverse distinction shall be made among prisoners on grounds of gender, religion, political opinion, nation, nationality, of social origin.

25. *Separate Accommodation*

1) Female prisoners shall have prison premises entirely separate from male prisoners.
2) To the extent that circumstances allow, prisoners shall have separte accommodation on the basis of age, offences and similar factors.

26. *Accommodation Standards*

1) Prison premises and compounds shall not be hazardous to health; and they shall have fresh air and sufficient lights.
2) without prejudice to Sub-Article 1 of this Article, prison premises shall have the due variation to accommodate prisoners with manifest behavioral reform and repentance, thereby motivating a positive spirit towards reform and rehabilitation.

27. *Food and Health Care*

Prisoners shall, free of charge, be provided with sufficient food and the necessary medical care and treatment that, as much as possible, enable the maintenance of their health.

28. *Female Prisoners Having Dependent Infants*

1) Where his interest so requires, a dependant infant not beyond eighteen months and that needs close maternal care may stay with his mother who is in custody.
2) The Commission shall provide what is necessary to the health and care of the infant.
3) Where the imprisonment of the mother is found to have an adverse physical or psychological impact on the infant, the commission shall facilitate the possibilities of finding a guardian or tutor to the infant.

29. *Access to visitors*

Prisoners shall have the right to communicate with their spouses, close relatives, friends, medical doctors, legal counselors and religious leaders. Particulars shall be determined by the Directives to be issued by the Commission.

30. *The right to impart information about imprisonment and transfer*

Every Prisoner shall have the right to promptly inform his family or any person of his imprisonment, or of his transfer on any ground from his current prison to another.

31. *Engagement in work and permission*

1) Every prisoner serving his sentence shall be assigned to work that suits his ability and vocation, and that does not affect his health; and shall receive remuneration for his work in accordannce with the Directives to be issued by the Commission.
2) The conditions of permission to enable prisoners settle various social problems with warden's escort shall be determined by directives.

፴፪· <u>የታራሚ ግዴታዎች</u>

ለጥበቃ ሥራ፣ ሥነ ሥርዓት አከባበር፣ ጽዳት፣ ጤና አጠባበቅ፣ ማኅበራዊ ግንኙነት እና ስለሌሎችም ጉዳዮች በሚወጣ ደንብ ወይም መመሪያ የሚገለጹ የሥነ ሥርዓት ግዴታዎችን ታራሚዎች የማክበር ግዴታ አለባቸው።

፴፫· <u>የወንጀል ድርጊት</u>

ማንኛውም ታራሚ በማረሚያ ቤት ቆይታው የወንጀል ድርጊት ቢፈጽም በወንጀል ሕግ ተጠያቂ ይሆናል።

<u>ክፍል አምስት</u>

<u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

፴፬· <u>ኮሚሽኑ ከክልል ማረሚያ ቤቶች ኃላፊዎች ጋር ስለሚኖረው የሥራ ግንኙነት</u>

፩· የማረሚያ ቤቶችን አስተዳደርና አሠራር፣ የታራሚ ዎችን አያያዝና አጠባበቅ ለማሻሻል፣ እንዲሁም ለማረሚያ ጥበቃ አባሎች እና ሠራተኞች የሥልጠና ዕድሎችን ለማመቻቸት፣ ከክልል ማረሚያ ቤቶች ኃላፊዎች ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

፪· ኮሚሽኑና የክልል ማረሚያ ቤት ኃላፊዎች በጋራ በሚወ ስኑት በማናቸውም ጊዜ የጋራ ጉባኤ ሊያካሂዱ ይችላል፣

፫· የጋራ ጉባኤውን የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽነር ይመራል፣

፬· የጋራ ጉባኤው፥—

ሀ) የጋራ የአሠራር ውስጠ ደንብ ያወጣል፣

ለ) የማረሚያ ቤቶች የሥራ እንቅስቃሴዎችን በመገ ምገም የልምድ ልውውጥ ያደርጋል፣ የአሠራር ደንብና መመሪያዎች በይዘት ረገድ እንዲሻሻሉና ወጥነት እንዲኖራቸው ያደርጋል፣

ሐ) የማረሚያ ጥበቃ የሥልጠናን አቅጣጫ ይዘትና ደረጃን በሚመለከት በጋራ ይቀይሳል፣

መ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በኮሚሽኑ በሚቀርቡ ጥናቶች ላይ ይወያያል፣ በጥናቶቹ መሠረት ሊወሰዱ የሚገ ባቸው እርምጃዎች እንዲወሰኑ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፣ እንደየሁኔታው በአግባቡ ይወስናል፣ በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል።

፭· ኮሚሽኑና የክልል የማረሚያ ቤቶች ኃላፊዎች በጋራ ጉባኤው ያስተላለፏቸው ውሳኔዎች መተግበራቸውን በየበኩላቸው ይከታተላሉ።

፮· የክልል ማረሚያ ቤቶች የታራሚዎችን አጠቃላይ ሁኔታ በሚመለከት ሪፖርትና ስታትስቲክስ በየጊዜው ለኮሚሽኑ ያስተላልፋሉ።

፴፭· <u>ወታደራዊ ማዕረግ ስለመቅረቱ</u>

፩· በማንኛውም ደረጃ የሚገኝ የማረሚያ ጥበቃ አባል ወታደራዊ ማዕረግ አይኖረውም፣ ሆኖም የማረሚያ ጥበቃ አባል የሆነ ማዕረግና ምልክት ይኖረዋል። ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፣

፪· ማንኛውም የማረሚያ ጥበቃ አባል የሥራ መደቡን የሚያመለክት የመለያ ደንብ ልብስ እንዲሁም ማንነቱን የሚገልጽ፣ ስሙን፣ መለያ ቁጥሩን፣ ክፍሉንና ኃላፊነቱን የያዘ ባጅ ወይም ምልክት ይኖረዋል።

፴፮· <u>አሠራር</u>

፩· በኮሚሽኑ መዋቅር በየደረጃው ባሉት ኃላፊዎችና ሠራተኞች የቡድን አሠራር ዋና ተግባር አፈጻጸም አቅጣጫ ይሆናል። የቡድን አሠራሮች የጋራና የነጠላ ኃላፊነትን ያስከትላሉ፣

፪· በኮሚሽኑ መዋቅር በየደረጃው የሚገኙ ኃላፊዎች በተሰ ጣቸው ሥልጣን መሠረት በመወሰን ኃላፊነታቸውን የመወጣት ግዴታ አለባቸው፣

32. *Obligations of prisoners*

Prisoners shall observe the desciplinary requirements stipulated by regulations or directives pertaining to custody, discipline, sanitation, health care, social life, and other issues.

33. *Criminal offence*

Any prisoner who commits a criminal offence while in custody shall be liable under criminal law.

PART FIVE

Miscellaneous Provisions

34. *Functional relations of the Commission with Regional Prison Authorities*

1) The Commission shall, have relations with Regional Prison Authorities in order to improve and enhance the administration modus operandi of prisons, the custody and treatment of prisoners, and also facilitate training opportunities to prison warden and other staff.
2) The Commission and Regional Prison Authorities may at any time hold the meeting of the Joint Council.
3) The Joint Council shall be presided by the Federal Prisons Commissiner.
4) The Joint Council shall:
   (a) issue Internal Regulations on mutual performance modalities;
   (b) share experience by reviewing the activities of prisons; cause the development and standardization of performance rules and directives with regard to their content;
   (c) jointly devise the direction, content and standard of prison wardens' training.
   (d) deliberate on the studies presented by the Commission in accordance with Article 8 Sub-Article (1) of this Proclamation; submit the studies to the competent organ for a decision on courses of action, or render decisions within the scope of its functions; and ensure their implementation.
5) The Commission and Regional Prison Authorities shall supervise the practical implementation of the decisions of the Joint Council in their respective organs.
6) Regional Prisons shall forward to the Commission priodic reports and statistics as regards the general condition of prisoners.

35. *Termination of military ranks*

1) No prison warden member of any hierarchy shall have a military rank. However, he shall have ranks and badge of the Prison warden. The particulars shall be determined by regulations.
2) Every prison warden shall have a uniform and a badge or sign that indicates his identity including his name, serial number, department and position.

36. *Performance modalities*

1) Teamwork shall be the principal pattern of performance by officials and employees at all levels of the Commission's structure. Teamwork shall entail joint and several responsibilities.
2) Officials of the Commission at all levels shall discharge their duties of decision-making in accordance with the powers entrusted to them.

፫· የኮሚሽኑ አሠራር የተጠያቂነትና የግልጽነትን መርህ የተከተለ፣ እንዲሁም የሕዝብ ተሳትፎን መሠረት ያደረገ መሆን ይኖርበታል።

## ፴፯· የተከለከለ ድርጊት

ማንኛውም ኢሰብአዊ ወይም ክብርን የሚነካ አያያዝ ወይም ድርጊት የተከለከለ ነው።

## ፴፰· የተሻሩ እና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች

፩· የወህኒ ቤቶች አስተዳደርን ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር ፵፭/፲፱፻፴፮ በዚህ አዋጅ ተሽሯል፣

፪· ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሌላ ሕግ በዚህ አዋጅ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

## ፴፱· ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

፩· የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የሚረዳ ደንብ ሊያወጣ ይችላል፣

፪· ኮሚሽኑ ይህን አዋጅ እና በአዋጁ መሠረት የሚወጣ ደንብን ለማስፈጸም የሚረዱ መመሪያዎችን የማውጣት ሥልጣን ይኖረዋል።

## ፵· አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከጳጉሜ ፬ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ·ም ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ጳጉሜ ፬ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ·ም

ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

3) The activities of the Commission shall pursue the principles of accountability and transparancy; and shall be based on popular participation.

37. *Forbidden acts*

Any treatment or act, that is inhuman or that violates human dignity is forbidden.

38. *Repealed and inapplicable laws*

1) The Prisons Administration Establishment Proclamation No. 45/1944 has been repealed by this Proclamation.
2) Any law which is inconsistent with this Proclamation shall not apply to matters provided for in this Proclamtion.

39. *Powers to issue regulations and directives*

1) The Council of Ministers may issue regulations for the implementation of this Proclamation.
2) The Commission shall have the power to issue directives for the implementation of this Proclamation and the Regulations issued there under.

40. *Effective Date*

This Proclamation shall come into force as of the 9th day of September, 2003.

Done at Addis Ababa, this 9th day of September, 2003.

GIRMA WOLDEGIORGIS
PRESIDENT OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA